የበዓሉ ግርማ በጎ አድራጎት ድርጅት እና የበዓሉ ቤተሰብ - እስከዛሬ ስለበዓሉ ሕይወት መጨረሻ በህግ የተጠና በቂ ማስረጃ እንዳልተገኘ ለማሳወቅ ይፈልጋሉ።

በዓሉ በጋዜጠኛነቱ፣ በመንግስት ስራውና በሕይወት ታሪኩ፣ የማይረሳ ኢትዮጵያዊ ነው። በዚህም ምክኒያት በዓሉ ግርማን በሚመለከት በየጊዜው የተለያዩ አስተያየቶችና ጽሁፎች ይቀርባሉ። የተከበራችሁ አንባቢያን እንደምታውቁት - የሰውን ታሪክ ለመፃፍ ትክክለኛ ምንጮችን መከተልና በቂ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ይጠይቃል። በዓሉ ግርማን ተመልክተው ለሚቀርቡትም ሥራዎች፣ አንባቢያን ይህንን ተገንዝበው፣ የሚያነቡትን ፈትነው፣ የራሳቸውን አስተያየት እንደሚወስዱ እናምናለን።

በዓሉ ግርማ ሀገሩን እና ቤተሰቡን የሚያፈቅር፣ ባጭር እድሜው ብዙ የስተዋለ ጸሀፊ ነበር። አንባቢያን በዓሉ የጻፋቸውን ድርሰቶችን በማንበብ፣ ስለደራሲው ብዙ እንደሚማሩ ተስፋ እናደርጋለን።

የበዓሉ ግርማ በጐ አድራጎት ድርጅት አላማው በዓሉ በሕይወት እያለ ያከብራቸው የነበሩትን መመሪያዎች መደገፍ ነው። እነዚሁም:- ድርሰትን ከልብ አፍቃሪ ወሆን፣ ሀገርን መውደድ እና በተጨማሪ የጋዜጠኝነትን ሙያ ዋና ተልእኮ መፈፀም ናቸው።

የበዓሉ ግርማ በጎ አድራጎት ድርጅት።